የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

ቁጥር አ1162/11/592

ቀን ሚያዝያ 19 ቀን 2014 ዓ.ም.

**ለብልፅግና ፓርቲ (ብልፅግና)**

**አዲስ አበባ፣**

መጋቢት 22 ቀን 2014 ዓ.ም. በቁጥር ብፓ/ምፕዋፅኃ/1062/14 በተፃፈ ደብዳቤ ከመጋቢት 2 እስከ መጋቢት 4 ቀን 2014 ዓ.ም. ፓርቲያችሁ ያደረገውን የፓርቲው 1ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ በሚመለከት የጉባኤውን ሪፖርት ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር ለቦርዱ አቅርቧል።

1. የብልፅግና ፓርቲ (ብልፅግና) አንደኛ ድርጅታዊ ጉባኤ ቃለ ጉባኤ ... 38 ገጽ
2. የብልፅግና ፓርቲ (ብልፅግና) መተዳደሪያ ደንብ (በብልፅግና ፓርቲ የመጀመሪያ ጉባኤ የፀደቀ) ... 31 ገጽ
3. የብልፅግና ፓርቲ (ብልፅግና) ፕሮግራም (በብልፅግና ፓርቲ የመጀመሪያ ጉባኤ የፀደቀ) ... 31 ገጽ
4. የብልፅግና ፓርቲ አንደኛ ጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴ የስራ ሪፖርት ... 9 ገጽ
5. የብልፅግና ፓርቲ የመጀመሪያ ጉባኤ ሰነድ... 96 ገጽ
6. የብልፅግና ፓርቲ የቁጥጥርና ኢንስፔክሽን ኮሚሽን የሥራ አፈፃፀም ምልከታና ምክረ ሃሣቦች ... 26 ገጽ
7. ብልፅግና ፓርቲ (ብልፅግና) የመጀመሪያ ድርጅታዊ ጉባኤ ላይ 1,656 ጉባኤተኞች ስለመገኘታቸው የፈረሙበት ሰነድ ... 112 ገጽ
8. የብልፅግና ፓርቲ (ብልፅግና) የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ዝርዝር ... 46 ገጽ
9. የብልፅግና ፓርቲ (ብልፅግና) ፓርቲ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትሙሉ ስም፣ አድራሻ እና በተመደቡበት የኃላፊነት ቦታ ላይ ለመሥራት የተስማሙ ስለመሆናቸው የሚገልፅ በፊርማቸው የተረጋገጠ ሰነድ ... 34 ገጽ
10. የብልፅግና ፓርቲ (ብልፅግና) ፓርቲ የቁጥጥርና ኢንስፔክሽን ኮሚቴ አባላት ዝርዝር ... 13 ገጽ
11. የብልፅግና ፓርቲ የመጀመሪያ ጉባኤ የአቋም መግለጫ ... 8 ገጽ

ለድምጽዎ የሚያምኑን



ፌስቡክ /national-electoal-board-of-ethiopia-nebe
ትዊተር @NEBEthiopia
ኢሜይል contact@nebe.org.et
ድረ-ገጽ www.nebe.org.et

አድራሻ - ቦሌ ክፍላሚንን
ሬስቶራንት ገባ ብሎ በስተቀኝ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

ስልክ +251 115 153468

ፋክስ +251 115 510025

ቦርዱ ሚያዝያ 13 ቀን 2014 ዓ.ም. ባካሄደው ስብሰባ ፓርቲው ያቀረባቸውን የጠቅላላ ጉባኤ ሰነዶች እና ጠቅላላ ጉባኤውን በታዘቡት የቦርዱ ተወካዮች የቀረበውን ሪፖርት መርምሯል። ይሁንና የጠቅላላ ጉባኤውን ሂደት፣ በጉባኤው የተላለፉ ውሳኔዎች እና የተደረጉ ምርጫዎችን በተመለከተ ከህጉ አንጻር ለመወሰን ተጨማሪ ሰነዶች እና መረጃዎችን ማየት አስፈልጓል።በመሆኑም ፓርቲው ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ***ከሚያዚያ 25 ቀን 2014 ዓ.ም በፊት*** ለቦርዱ እንዲያቀርብ እናሳውቃለን፡

**ቃለ ጉባኤን በተመለከተ፡-**

1ኛ/ በጠቅላላ ጉባኤ ቃለ ጉባኤው ላይ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባው ምልአተ ጉባኤ ተሟልቷል ቢባልም በግልፅ የጠቅላላ ጉባኤው ተሳታፊ አባላት ብዛት ስላልተቀመጠ ተገልፆ እንዲቀርብ፤

2ኛ/ የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት የተጠቆሙበት ሂደት፣ እነማን እንደተጠቆሙ፣ ከተጠቆሙት ውስጥ የተመረጡት አባላት እያንዳንዳቸው በስንት ድምፅ እንደተመረጡ በጠቅላላ ጉባኤ ቃለ ጉባኤ ውስጥ ያልተገለፀ በመሆኑ ይሄው ተካቶ እና ተረጋግጦ እንዲቀርብ፤

3ኛ/ በፓርቲው የቀረበው የጠቅላላ ጉባኤ ቃለ ጉባኤ በፓርቲው ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተፈርሞ እንዲቀርብ፤

4ኛ/ የማዕከላዊ ኮሚቴው የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትን የመረጠበትን ሂደት የሚያሳይ የማዕከላዊ ኮሚቴ ቃለ ጉባኤ ስላልቀረበ እንዲቀርብ፤

**የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብን በተመለከተ፡-**

1ኛ/ በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀፅ 18/3 መሠረት የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ብዛትና ስብጥርን በተመለከተ የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ ካለ የመመሪያውን ኮፒ ማዕከላዊ ኮሚቴው መመሪያውን ካፀደቀበት ቃለ ጉባኤ ጭምር እንዲቀርብ፤

2ኛ/ በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀፅ 18/8/ሠ መሠረት ስለምርጫ ስርዓት ማለትም ፓርቲውን ወክለው በምርጫ የሚሳተፉ አባላትን ስለሚመመረጡበት ሁኔታ በማዕከላዊ ኮሚቴው የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ ካለ ማዕከላዊ ኮሚቴው መመሪያውን ካፀደቀበት ውሣኔ ቃለ ጉባኤ ጋር አብሮ እንዲቀርብ፤

3ኛ/ በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀፅ 23/1 መሠረት የኢንስፔክሽንና ቁጥጥር ኮሚቴ አባላት ብዛትና ስብጥርን በተመለከተ በማዕከላዊ ኮሚቴ የወጣ መመሪያ ካለ መመሪያው ከጸደቀበት ቃለ ጉባኤ ጋር አብሮ እንዲቀርብ፤

4ኛ/ በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀፅ 32/1 ከፓርቲው ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት ውጭ ላሉ ሌሎች አመራሮች የኃላፊነት ዘመን ለመወሰን የማዕከላዊ ኮሚቴው ያወጣው መመሪያ ካለ መመሪያውን የያዘ ቃለ ጉባኤ ከመመሪያው ጋር አብሮ እንዲቀርብ፤

**ሌሎች፡-**

የጉባኤው የስብሰባ ስነ ስርዓት ደንብ በማን እንደፀደቀ ከሚገልፅ ማብራሪያ ጋር እንዲቀርብ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ያሳውቃል።

ከበጎ ምኞት ጋር

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
የፖለቲካ ፓርቲዎች ዘርፍ

ብርቱካን ሚደቅሳ
የኢትዮጵያ ብሔራዊ
ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ